**የዲሲ መንግስት (GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA)**

የጤና ክብካቤ ፋይናንስ መምሪያ (Department of Health Care Finance)

**ለነፍሰ ጡር ግለሰቦች የጤና እንክብካቤ ሽፋን**

እርግዝና በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች (በየጥ(FAQ))

**ዓላማው፤** የዚህ ሰነድ አላማ ስለ እርጉዝ ግለሰቦች የጤና እንክብካቤ ሽፋን መረጃ መስጠት ነው።

**<u>የፕሮግራሙ አጠቃላይ ዕይታ</u>**

**1. ለነፍሰ ጡር ግለሰቦች የብቁነት መስፈርቶች ምንድን ናቸው?**

ዲስትሪክቱ ለነፍሰ ጡር ሴቶች የጤና ሽፋን **<u>ሁለት</u>** መንገዶች አሉት **በ ሲኤችአይፒ ከመፀነስ እስከ እርግዝና መጨረሻ (CHIP From Conception to End of Pregnancy (ኤፍሲኢፒ (FCEP)) አማራጭ** ፤ ሲኤችአይፒ ያልተወለደ ልጅ (CHIP Unborn Child) በማለት የሚታወቀው ማለት ነው፤ እና **በሜዲኬይድ (Medicaid)** በኩል። የብቃት መስፈርት ከዚህ በታች ይመልከቱ:

**<u>(CHIP From Conception to End of Pregnancy (ኤፍሲኢፒ (FCEP))</u>**

- እርጉዝ
- የዲሲ ነዋሪ
- የስደት ሁኔታ ምንም ይሁን ምን
- የገቢ መስፈርቶችን ማሟላት
- ለሜዲኬይድ (Medicaid) ወይም ሜዲኬር (Medicare) ያልተመዘገበ ወይም ብቁ ያልሆነ

**<u>ሜዲኬይድ (Medicaid) ፕሮግራም</u>**

- እርጉዝ
- የዲሲ ነዋሪ
- የአሜሪካ ዜጋ ወይም ብቁ የሆነ የስደት ሁኔታ
- የገቢ መስፈርቶችን ማሟላት

**2. ለነፍሰ ጡር ግለሰቦች የገቢ ገደቦች ምን ያህል ናቸው?**

| ምድብ | ነፍሰ ጡር ግለሰብ |
|---|---|
| **ገደብ (Threshold) ኤፍፒኤል (FPL) ውስጥ** | 319% + 5% መተው (disregard) |
| **ባለ 2 ሰው ቤተሰብ፤ ወርሃዊ** | $5,712 |
| **ባለ 3 ሰው ቤተሰብ፤ ወርሃዊ** | $7,196 |

# ለነፍሰ ጡር ግለሰቦች የጤና ሽፋን – በየጥ ቪ.1.1 (FAQ v1.1)

| | |
|---|---|
| **ባለ 4 ሰው ቤተሰብ፤ ወርሃዊ** | $8,683 |
| **ባለ 5 ሰው ቤተሰብ፤ ወርሃዊ** | $10,167 |
| **ባለ 6 ሰው ቤተሰብ፤ ወርሃዊ** | $11,651 |
| **ባለ 7 ሰው ቤተሰብ፤ ወርሃዊ** | $13,138 |
| **ባለ 8 ሰው ቤተሰብ፤ ወርሃዊ** | $14,622 |

**3. ነፍሰ ጡር ከሆንኩ ለጤና ሽፋን ለማመልከት የዕድሜ መስፈርት አለ?**

ንአይ፣ ለእርግዝና የጤና ሽፋን በሲኤች አይፒ ከጽንስ እስከ እርግዝና መጨረሻ (CHIP From Conception to End of Pregnancy (ኤፍሲፒ(FCEP))) ወይም ሜዲኬይድ (Medicaid) በኩል ለሚያመለክቱ ግለሰቦች የዕድሜ ገደብ የለም።

**4. ነፍሰ ጡር መሆኔን እንዴት ሪፖርት አደርጋለሁ?**

እንደ ዲስትሪክት ዳይረክት (District Direct) ፣ ስልክ፣ ፋክስ፣ ፖስታ ወይም በአካል ባሉ በሁሉም ዘዴዎች እርግዝናዎን ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ። ማድረግ ያለብዎት እርጉዝ መሆንዎን እና የሚተበቀውን የመውለጃ ቀን (ወይም የተፀነሰበት ቀን) ሪፖርት ማድረግ ብቻ ነው። ምንም ተጨማሪ ማረጋገጫ አያስፈልግም.

**5. በአሁኑ ጊዜ የጤና እንክብካቤ አሊያንስ (Health Care Alliance) እየተቀበልኩ ነው፣ እና ነፍሰ ጡር ነኝ የጤና ሽፋኑ በ9/30/2025 ይዘጋል?**

እርጉዝ መሆንዎን እና የሚጠበቀውን የመውለጃ ቀን (ወይም የተፀነሰበት ቀን) ሪፖርት ማድረግዎን ያረጋግጡ። ይህ ሪፖርት ከቀረበ በኋላ፣ ብቁነትዎ ከጤና ክብካቤ አሊያንስ (Health Care Alliance) ወደ ሜዲኬይድ (Medicaid) ወይም ሲኤችአይፒ ከመፀነስ ወደ እርግዝና መጨረሻ (CHIP From Conception to End of Pregnancy (FCEP)) ይቀየራል።

**6. አሁን ነፍሰ ጡር ከሆንኩ ግን የጤና እንክብካቤ አሊያንስ (Health Care Alliance) ወይም ሜዲኬይድ (Medicaid) ከሌለኝ እንዴት የጤና ሽፋን ማግኘት እችላለሁ?**

ለጤና ሽፋን ማመልከቻ በዲስትሪክት ዳይሬክት (District Direct) ፣ በስልክ፣ በፋክስ፣ በፖስታ ወይም በአካል በመቅረብ እርጉዝ መሆንዎን መግለጽዎን እና የሚጠበቀውን የመውለጃ ቀን ማስገባትዎን ያረጋግጡ። ገቢን ጨምሮ ሁሉም ሌሎች የብቃት ሁኔታዎች መቅረብ አለባቸው እና እርስዎ ይገመገማሉ። ብቁ ከሆነ ሽፋንዎ ማመልከቻው ከገባበት የመጀመሪያ ወር ይጀምራል።

**7. የእርግዝናዬ የጤና እንክብካቤ ሽፋን የሚጀምረው እና የሚያበቃው መቼ ነው?**
እንደ መርሃግብሩ ይለያያል። ከዚህ በታች ያሉትን ልዩነቶች ይመልከቱ፤

<u>ሲኤችአይፒ ከመፀነስ ወደ እርግዝና መጨረሻ (CHIP From Conception to End of Pregnancy (FCEP)</u>

- ለእርግዝና ብቁነት፤ እርግዝናው ሪፖርት ከተደረገበት የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ እስከ እርግዝናው ማብቂያ።
- ከወሊድ በኋላ የሚደረግ እንክብካቤ (ከወሊድ በኋላ ያለው ጊዜ)፤ እርግዝናው ካለቀ በኋላ ለ (2) ወራት።

ምሳሌ፤ ሱ (Sue) እርጉዝ ነች እና ለጤና ሽፋን አመልክታለች። የመውለጃ ቀኗ 3/5/2026 ነው። ማመልከቻዋ ከ 9/2025 ጀምሮ ለ ሲኤችአይፒ ከመፀነስ ወደ እርግዝና መጨረሻ (CHIP From Conception to End of Pregnancy (FCEP) ጸድቋል። በ 3/4/2026 የእርግዝና መጨረሻን ሪፖርት አድርጋለች። • ከወሊድ በኋላ የሚደረግ ሽፋን በ 4/1/2026 ጀምሮ በ 5/31/2026 ያበቃል።

<u>ሜዲኬይድ (Medicaid) ፕሮግራም</u>

- ለእርግዝና ብቁነት፤ እርግዝናው በሚጀምርበት የመጀመሪያ ቀን ይጀምራል እና እስከ እርግዝና መጨረሻ ድረስ ይቆያል።
- ከወሊድ በኋላ የሚደረግ እንክብካቤ (ከወሊድ በኋላ ያለው ጊዜ)፤ እርግዝናው ካለቀ በኋላ ለ አስራ ሁለት (12) ወራት

ምሳሌ፤ አሽሌ (Ashley) እርጉዝ ነች እና ለጤና ሽጋን አመልክታለች። የመውለጃ ቀኗ 3/5/2026 ነው። ማመልከቻዋ ለሜዲኬይድ (Medicaid) ከ 9/2025 ጀምሮ ጸድቋል። የእርግዝና ማብቂያን በ 3/4/2026 ሪፖርት አድርጋለች። ከወሊድ ብኋላ የሚደረግ ሽፋን በ 4/1/2026 ጀምሮ በ 3/31/2027 ያበቃል።

**8. ሲኤችአይፒ ከመፀነስ ወደ እርግዝና መጨረሻ (CHIP From Conception to End of Pregnancy (FCEP) ወሊድን (delivery) ይሸፍናል?**

አዎ።

**9. ሲኤችአይፒ ከመፀነስ ወደ እርግዝና መጨረሻ (CHIP From Conception to End of Pregnancy (FCEP) ወይም ሜዲኬይድ (Medicaid) ፕሮግራም በማኔጅድ ኬር (managed care) ወይም ፊ ፎር ሰርቪስ (fee for service) ነው?**

ማኔጅድ ኬር (Managed Care)።

**10. ከኦክቶበር 1, 2026 በኋላ ለእርግዝና የጤና ሽፋን ካመለከትኩ እና ከ26 በላይ ሆኜ ወይም ገቢዬ ከ138% ኤፍፒኤል (FPL) በላይ ከሆነ ምን ይከሰታል?**

**ለ ሲኤችአይፒ ከመፀነስ ወደ እርግዝና መጨረሻ** (**CHIP From Conception to End of Pregnancy (FCEP) ብቁ ከሆኑ፤** እስከ እርግዝናዎ መጨረሻ ድረስ በሽፋን ውስጥ ይመዘገባሉ። እርግዝናዎ ካለቀ በኋላ ሁለት (2) ተጨማሪ ወራት ያገኛሉ ከዚያም ሽፋንዎ ይቋረጣል።

*ምሳሌ፤* ኬሊ (Kelly) 28 ዓመቷ ነው፤ እርጉዝም ነች። በኦክቶበር 15 2025 ለጤና ሽፋን አመልክታለች፤ እናም ህሉንም የብቃት መስፈርቶች አሟልታ ለሲኤችአይፒ ከመፀነስ ወደ እርግዝና መጨረሻ (CHIP From Conception to End of Pregnancy (FCEP) ብቁ ናት። እርግዝናዋ በፌብሩዋሪ 2፣ 2026 ያበቃል። ከማርች 2026 እስከ ኤፕሪል 2026 ተጨማሪ የጤና ሽፋን ይኖራታል። ብቁነቷ ኤፕሪል 30፣ 2026 ያበቃል።

*ማስታወሻ: እርግዝናው ካለቀ በኋላ በጤና እንክብካቤ አሊያንስ (Health Care Alliance) አትመዘገብም ምክንያቱም በእድሜዋ ምክንያት ብቁ ስላልሆነች ነው። የጤና እንክብካቤ አሊያንስ (Health Care Alliance) ከኦክቶበር 1፣ 2025 ጀምሮ ዕድሜያቸው 26 ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ እና/ወይም ከ138% በላይ ገቢ ያላቸውን ተመዝጋቢዎችን አይቀበልም።

**ለ ሜዲኬይድ (Medicaid) ብቁ ከሆኑ፣** እርግዝናዎ እስኪያልቅ ድረስ በሽፋን ውስጥ ይመዘገባሉ። አንዴ እርግዝናዎ ካለቀ በኋላ ተጨማሪ አስራ ሁለት (12) ወራት የጤና ሽፋን ያገኛሉ ከዚያም ለቀጣይ ሜዲኬይድ ወይም ሽፋን በዲሲ ሄልዝ ሊንክ (DC Health Link) በኩል ይገመገማሉ።

*ምሳሌ 1*፤ ዳውን (Dawn) 28 ዓመቷ ነው፤ እርጉዝ ናት። በኦክቶበር 15፣ 2025 ለጤና ሽፋን ታመለክታለች፣ እና ሁሉንም የብቃት መስፈርቶች አሟልታለች እና ለሜዲኬይድ (Medicaid) ብቁ ናት። እርግዝናዋ ፌብርዋሪ 2, 2026 ያበቃል። ከማርች 2026 እስከ ፌብርዋሪ 2027 ተጨማሪ የጤና ሽፋን ታገኛለች። በሁሉም የብቃት ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ በ ፌብርዋሪ 2027 የእውቅና ማረጋገጫ ጊዜዋ መጨረሻ ላይ ለሜዲኬድ ብቁ ትሆናለች። ለሜዲኬይድ (Medicaid) ለተጨማኢ አንድ ዓመት ይታደስላታል።

*ምሳሌ 2*፤ ዳውን (Dawn) 28 ዓመቷ ነው፤ እርጉዝ ናት። በኦክቶበር 15፣ 2025 ለጤና ሽፋን ታመለክታለች፣ እና ሁሉንም የብቃት መስፈርቶች አሟልታለች እና ለሜዲኬይድ (Medicaid) ብቁ ናት። እርግዝናዋ ፌብርዋሪ 2, 2026 ያበቃል። ከማርች 2026 እስከ ፌብርዋሪ 2027 ተጨማሪ የጤና ሽፋን ታገኛለች። በሁሉም የብቃት ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ፤ በ ፌብሯሪ 2027 የማረጋገጫ ጊዜዋ መጨረሻ ባገባችው ገቢ ምክንያት ለሜዲኬይድ (Medicaid) ብቁ አይደለችም፤ እና በፌብርዋሪ 2027 መጨረሻ ላይ ይቋረጣል። ለማርኬት ፕሌስ ኢንሹራንስ (marketplace insurance) ግምገማ ወደ ዲሲ ሄልዝ ሊንክ (DC Health Link) ትላካለች።

**11. ሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan) እርጉዝ የሆኑ ግለሰቦችን ይሸፍናል?**

አይ። ከ 1/1/2026 ጀምሮ በሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan) ላይ ተሳታፊ ከሆኑ እና ከፀነሱ እርግዝናዎን ወዲያውኑ ለዲሲ ሄልዝ ሊንክ (DC Health Link) ሪፖርት ያድርጉ። አንዴ እርግዝናዎ ሪፖርት ከተደረገ፣ ለ ሲኤችአይፒ ከመፀነስ ወደ እርግዝና መጨረሻ (CHIP From Conception to End of Pregnancy (FCEP)) ወይም ሜዲኬይድ (Medicaid) ይገመገማሉ።

**12. ለነፍሰ ጡር ግለሰቦች በ ሲኤችአይፒ ከመፀነስ ወደ እርግዝና መጨረሻ (CHIP From Conception to End of Pregnancy (FCEP)) ወይም ሜዲኬይድ (Medicaid) ላይ ምን ዓይነት አገልግሎቶች ተሸፍነዋል?**

ሲኤችአይፒ ከመፀነስ ወደ እርግዝና መጨረሻ (CHIP From Conception to End of Pregnancy (FCEP)) እና ሜዲኬይድ (Medicaid) በስቴት ፕላን (State Plan) ስር ያሉትን ሁሉንም የጤና አገልግሎቶች ይሰጣሉ።